የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ

# ፌዴራል ነጋሪት ጋዜጣ

# FEDERAL NEGARIT GAZETA

OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA

አሥራአምስተኛ ዓመት ቁጥር ፱
አዲስ አበባ ታህሣሥ ፲፮ ቀን ፪ሺ፩ ዓ.ም

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ጠባቂነት የወጣ

15th Year No. 9
ADDIS ABABA 25th December, 2008

ማውጫ

CONTENTS

አዋጅ ቁጥር ፮፻፲፪/፪ሺ፩ ዓ.ም

የቴምብር ቀረጥ /ማሻሻያ/ አዋጅ … ገጽ ፬ሺ፫፻፹፱

Proclamation No. 612/2008

Stamp Duty (Amendment) Proclamation Page 4389

## አዋጅ ቁጥር ፮፻፲፪/፪ሺ፩

## የቴምብር ቀረጥ አዋጅን ለማሻሻል የወጣ አዋጅ

የቴምብር ቀረጥ አዋጅ ቁጥር ፩፻፲/፲፱፻፺ን ማሻሻል አስፈላጊ ሆኖ በመገኘቱ፣

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሕገ መንግሥት አንቀጽ ፶፭ ንዑስ አንቀፅ (፩) እና /፲፩/ መሠረት የሚከተለው ታውጇል።

**፩. አጭር ርዕስ**

ይህ አዋጅ "የቴምብር ቀረጥ /ማሻሻያ/ አዋጅ ቁጥር ፮፻፲፪/፪ሺ፩" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል።

**፪. ማሻሻያ**

የቴምብር ቀረጥ አዋጅ ቁጥር ፩፻፲/፲፱፻፺ እንደሚከተለው ተሻሽሏል፣

፩/ በአዋጁ ውስጥ በማናቸውም ሥፍራ "የፌዴራል አገር ውስጥ ገቢ ባሥልጣን" ወይም "የፌዴራል ገቢዎች ቦርድ" የሚለው ስያሜ ተሰርዞ "የኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለሥልጣን" በሚለው ተተክቷል።

## PROCLAMATION NO. 612 /2008.

## A PROCLAMATION TO AMEND THE STAMP DUTY PROCLAMATION

**WHEREAS,** it has become necessary to amend the Stamp Duty Proclamation N0. 110/1998;

**NOW, THEREFORE,** in accordance with Article 55 (1) and (11) of the Constitution of the Federal Democratic Republic of Ethiopia it is hereby proclaimed as follows:

**1. Short Title**

This Proclamation may be cited as the "Stamp Duty (Amendment) Proclamation No. 612/2008".

**2. Amendment**

The Stamp Duty Proclamation No. 110/1998 is hereby amended as follows:

1/ The reference to the "Federal Inland Revenue Authority" or to the "Federal Government Revenues Board" anywhere in the Proclamation is repealed and replaced by the "Ethiopian Revenues and Customs Authority".

፪/ የአዋጁ አንቀጽ ፱ ተሰርዞ በሚከተለው አዲስ አንቀጽ ፱ ተተክቷል፣

"፱. <u>ይግባኝ የማቅረብ መብት</u>

የኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለሥልጣን በወሰነው የቴምብር ቀረጥ መጠን ላይ የማይስማማ ቀረጥ ከፋይ ባለሥልጣኑ ውሳኔውን በጽሁፍ ካስታወቀበት ቀን አንስቶ በ፴ ቀናት ውስጥ ቅሬታውን ለአቤቱታ አጣሪ ቡድን ወይም ለግብር ይግባኝ ሰሚ ጉባኤ ማቅረብ ይችላል። "

፫/ ከአዋጁ አንቀጽ ፱ ቀጥሎ የሚከተሉት አዲስ አንቀጽ ፲፣ ፲፩፣ እና ፲፪ ተጨምረዋል፣

"፲. <u>መቀጫን ስለማንሳት</u>

በቀረጥ ከፋይ ላይ የተጣለ አስተዳደራዊ መቀጫ የኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለሥልጣን በሚያወጣው መመሪያ መሠረት በሙሉ ወይም በከፊል እንዲነሳ ለማድረግ ይቻላል።

፲፩.<u>ለግብር ይግባኝ ጉባኤ ስለሚቀርብ ይግባኝ</u>

፩/ በማንኛውም የቴምብር ቀረጥ አወሳሰን ቅር የተሰኘ ግብር ከፋይ ለግብር ይግባኝ ጉባኤ ይግባኝ ማቅረብ ይችላል።

፪/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ /፩/ መሠረት የሚቀርብ ይግባኝ፣

ሀ/ ቀረጥ ከፋዩ አከራካሪ የሆነውን የቴምብር ቀረጥ መጠን ሃምሳ በመቶ ለኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለሥልጣን ካላስያዘ፣ እና

ለ/ የቀረጥ ውሳኔ ማስታወቂያው ወይም በአቤቱታ አጣሪ ቡድን የተሰጠው ውሳኔ ለግብር ከፋዩ በደረሰው በ፴ ቀን ውስጥ ካልቀረበ፣ በግብር ይግባኝ ጉባኤው ተቀባይነት አይኖረውም።

፫/ በገቢ ግብር አዋጅ ቁጥር ፪፻፹፮/፲፱፻፺፬ ስለይግባኝ የተደነገጉት እንደ አግባብነታቸው በዚህ አዋጅ መሠረት ለሚቀርብ ይግባኝም ተፈፃሚ ይሆናሉ።



2/ Article 9 of the Proclamation is repealed and replaced by the following new Article 9:

**"9. <u>Right to Appeal</u>**

Any person who is dissatisfied with the amount of stamp duty assessed by the Ethiopian Revenues and Customs Authority may, within 30 days of the receipt of the assessment notifications, appeal to the Review Team or the Appeal Commission against the assessment."

3/ After Article 9 of the Proclamation the following new Articles 10, 11, and 12 are added:

**"10. <u>Waiver of Penalty</u>**

Administrative penalties may be waived wholly or partly in accordance with the directives issued by the Ethiopian Revenues and Customs Authority.

**11.<u>Appeals to the Tax Appeal Commission</u>**

1/ Any taxpayer who objects to an assessment of stamp duty may appeal to the Tax Appeal Commission.

2/ No appeal, under sub-article (1) of this Article, may be accepted by the Tax Appeal commission unless:

a) a deposit of 50% of the disputed amount is made to the Ethiopian Revenues and Customs Authority; and

b) the appeal is lodged within 30 days following the day of receipt of the assessment notice or the decision of the Review Team.

3/ The provisions of the Income Tax Proclamation No. 286/2002 relating to appeals shall, mutatis mutandis, apply to appeals submitted under this Proclamation.

## ፲፪. <u>የግብር ይግባኝ ጉባኤ ውሳኔን በመ ቃወም ስለሚቀርብ ይግባኝ</u>

፩/ የይግባኝ ጉባኤ የሰጠው ውሳኔ በሕግ ረገድ ስህተት ነው በማለት ያልተስማማ ማንኛውም ተከራካሪ ወገን የግብር ይግባኝ ጉባኤው ውሳኔ በደረሰው በ፴ ቀናት ውስጥ ሥልጣን ላለው ይግባኝ ሰሚ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሊያቀርብ ይችላል።

፪/ ይግባኝ ሰሚው ፍርድ ቤት በሕግ ረገድ የተነሳውን ክርክር መር ምሮ ውሳኔ በመስጠት ጉዳዩን ለግ ብር ይግባኝ ጉባኤው ይመልስ ለታል።

፫/ በይግባኝ ሰሚው ፍርድ ቤት ውሳኔ ቅር የተሰኘ ወገን ውሳኔው በተሰጠ በ፴ ቀን ውስጥ ለበላይ ይግባኝ ሰሚ ፍርድ ቤት ይግባኝ ማቅረብ ይችላል።"

፬/ የአዋጁ የቀድሞ አንቀጽ ፲፣ ፲፩፣ ፲፪፣ ፲፫፣ ፲፬ እና ፲፭ አንቀጽ ፲፫፣ ፲፬፣ ፲፭፣ ፲፮፣ ፲፯ እና ፲፰ ሆነዋል።

## ፫. <u>አዋጁ የሚፀናበት ጊዜ</u>

ይህ አዋጅ በፌዴራል ነጋሪት ጋዜጣ ታትሞ ከወጣበት ቀን ጀምሮ የፀና ይሆናል።

**አዲስ አበባ ታህሣሥ ፲፮ ቀን ፪ሺ፩ ዓ.ም**

**ግርማ ወልደጊዮርጊስ**

**የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ፕሬዚዳንት**

## 12. <u>Appeals against Decisions of the Tax Appeal Commission</u>

1/ Any party dissatisfied with the decision of the Tax Appeal Commission may appeal to the competent court of appeal on the ground that it is erroneous on any matter of law within 30 days from the date of receipt of the decision of the Tax Appeal Commission.

2/ The court of appeal shall hear and determine the question of law arising from the appeal and return the case to the Tax Appeal Commission.

3/ Any party who is dissatisfied with the decision of the appellate court may make an appeal to the next court of appeal within 30 days from the date of the decision."

4/ The former Articles 10, 11, 12, 13, 14, and 15 of the Proclamation are renumbered as Articles 13, 14, 15, 16, 17 and 18 respectively.

## 4. <u>Effective Date</u>

This Proclamation shall enter into force up on the date of publication in the Federal Negarit Gazeta.

**Done at Addis Ababa, this 25th day of December, 2008**

**GIRMA WOLDEGIORGIS**

**PRESIDENT OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA**